טיפות 2

# ሁለት ጠብታ ብቻ
## እና ከፖሊዮ በሽታ አደገኝነት ቤተሰቡ የተጠበቀ ይሆናል

**የጤና ሚኒስተር የፖሊዮ ቫይረስ ለመከላከል ሕብረተሰቡን ለመጠበቅ በሚል ዓላማ የክትባት ርብርብ ግብረት እያደረገ ነው።**

እንደ ጤና ሚኒስተር መመሪያ መሠረት ክትባቱ
የሚሰጠው በጠብታ (OPV) አማካኝነት ነው።
ሁሉም ልጅ (ከጥር 1 2004 እ.ኤ.አ ጀምሮ ለተወለዱ ልጆች ነው)
ክትባቱም ያለ አንዳች ክፍያ (በነፃ) ይሰጣል
ዓላማው ቤተሰቡ በዚህ በሽታ ልክፈት እንዳይያዝ ለመከላከል ነው።

קול הבריאות *5400
מוקד טלפוני אחד לכל יחידות משרד הבריאות

משרד הבריאות
לחיים בריאים יותר

# አደገኛ ውሳኔ አይውሰዱ ክትባት ይከተቡ

ክትባቱን ለመከተብ እና ተጨማሪ መረጃ
ለመቀበል — ቲፓት ሐላቭ ጣቢያ ወይም
የጤና ሚኒስተር የኢንተርኔት ድረ ገጽ
መመልከት እና መጎብኘት ይቻላል።
www.health.gov.il

אמהרית

קול הבריאות *5400
מוקד טלפוני אחד לכל יחידות משרד הבריאות

משרד הבריאות
לחיים בריאים יותר

חפשו אותנו ב-

# አደገኛ ውሳኔ አይውሰዱ ክትባት ይከተቡ

## የፖሊዮ በሽታ ምንድር ነው?

የፖሊዮ በሽታ ማለት ፖሊዮ ከሚባል ቫይረስ ሳቢያ የሚከሰት የልጅነት ልምሻ በሽታ ነው። ይህ ቫይረስ ከሰው ወደ ሰው (ይልቁንም በልጆች መካከል) የሚተላለፍ በሽታ ነው።

ይህ ቫይረስ በአንደበት (በአፍ) በኩል ወደ ሰውነት የሚገባ እና በሰገራ በኩል ከሰውነት የሚወጣ ቫይረስ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የበሽታው መለያ ምልክቶች የሉትም በመሆኑም ከአንድ ሺህ ሰዎች መካከል አንድ ሰው ብቻ (ክትባቱን ያልወሰዱ ሰዎች) በበሽታው በመታመም የአካል መተሳሰር (የአጥንት ልምሻ) ሊያስከትልበት ይችላል።

## በዚህ በሽታ ላለመያዝ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

በጣም ጠቃሚ እና አስፈላጊ ሊያደርጉ የሚገባዎት ክትባት መከተብ ነው። ከዚህ ክትባት ባሻገር ንጽሕናን በሚገባ በመጠበቅ

በይበልጥ ደግሞ ከመጻዳጃ ቤት ሲወጡ ወይም የሕፃን የሽንት ጨርቅ ከቀየሩ

በኋላ እንዲሁም ምግብ ከመንካትዎ በፊት ለ20- ሰከንድ ያህል እጅዎትን በውኃ እና በሳሙና መታጠብ ተገቢ ነው።

## ለዚህ በሽታ የተጋለጠ እንዲሁም በሽታውን መቋቋም የሚችል ሰው ማነው?

አብዛኛውን የእስራኤል አገር ነዋሪዎች (ሕፃናት እና አዛውንቶች) የፖሊዮ በሽታን ለመከላከል ክትባት የተከተቡ ሰዎች።

ይህን ክትባት ያልተከተቡ ሰዎች አሉ፦ ለምሳሌ ያህል በቲፓት ሐላቭ የሕፃናት ክትባታቸውን ያልጨረሱ ህፃናት፣ በበሽታ ወይም በተለየ ሕክምና ምክንያት በሽታን የመቋቋም አቅማቸው የተዳከመ ልጆች እና አዛውንቶች እንዲሁም ከዚህ በፊት ክትባት የተከተቡ አዛውንቶች ቢሆኑም ነገር ግን የፖሊዮ በሽታን የመቋቋም አቅማቸው እየተዳከመ የመጣ ሰዎች ናቸው።

## የጤና ሚኒስተር ምን እንዲያደርጉ ይመክራል?

የጤና ሚኒስተር የፖሊዮ በሽታን ለመከላከል ሕብረተሰቡን ለመጠበቅ በሚል ዓላማ የክትባት ርብርብ እያደረገ ነው።

የጤና ሚኒስተር መመሪያ ከጥር 2004 1 እ.ኤ.አ ጀምሮ ለተወለዱ ሕፃናት **እያንዳንዱ ልጅ** ክትባቱን እንዲከተቡ ነው። ይህ ክትባት ከዚህ ቀደም ልጆቹ ክትባት ሲከተቡበት በነበረው ቲፓት ሐላቭ ወይም ልጆቹ ከዚህ በፊት ክትባት ተቀብለው የማያውቁ ከሆነ በመኖሪያ ቦታቸሁ በአቅራቢያ ወደ ሚገኘው ቲፓት ሐላቭ በመሄድ ነው።

ቲፓት ሐላቭ ከአሁኑ መንግስታዊ ርብርብ ግብረት ጋር ባልተያያዘ መልኩ ሁል ጊዜ የፖሊዮ በሽታን መከላከያ የሞተ የፖሊዮ ቫይረስን (IPV) የሚል ስያሜ ያለው በክትባት በመርፌ አማካኝነት በሁለት ወሩ፣ በአራት ወሩ፣ በግማሽ ዓመቱ፣ በአንድ ዓመቱ እና የሁለተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በልጁ የሕይወት ዘመኑ ለአምስት ጊዜ ያህል ክትባቱን ይከተባል።

ከዚህ በፊት ቢያንስ አንድ ጊዜ እንኳን የፖሊዮ ክትባት (IPV) በመርፌ የተከተበ ከሆነ አሁን የሚሰጠውን ክትባት ደግሞ ኃይሉ የተዳከመውን የፖሊዮ ቫይረስ ክትባት (bOPV) የተሰኘውን በአፍ በኩል የሚሰጥ ሁለት ጠብታ እና የሞተ የፖሊዮ ቫይረስ (IPV) በመርፌ ክትባት ጋር ይሰጠዋል። የሞተ የፖሊዮ ቫይረስ (IPV) ክትባትን ያልተከተበ ልጅ ካለ ይህንኑ ክትባት እንዲከተብ ይደረጋል።

## አስፈላጊነቱ ምንድር ነው?

የጤና ሚኒስተር የእሰራኤል አገር የቆሻሻ ቱቦዎች ላይ ምርመራ ያደርጋል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ በደቡብ እስራኤል በምትገኘው ረሃት ከተማ ውስጥ የቆሻሻ ትቦ ውስጥ የፖሊዮ ቫይረስ በመገኘቱ ምክንያት በሌሎች ስፍራ በተደረገው ምርመራ በተለያዩ ደቡባዊ መንደሮች እና ከተሞች፦ በራምሌ፣ በሉድ፣ በኸደራ ከተማ አጠገብ በሚገኘው ባካ ኤል ጋርብያ እንዲሁም በኸደራ እና በሻሮን ከተሞች አካባቢ በተለያዩ ቦታዎች ይህ ቫይረስ ተገኝቷል። ስለዚህ የጤና ሚኒስተር ኃይሉ የተዳከመውን የፖሊዮ ቫይረስ ክትባት (OPV) እንዲከተቡ ወስኖአል። የዚህ ክትባት ዓላማው ይህ ቫይረስ በአገሪቱ በሙሉ እንዳይሰራጭ በማሰብ እና ቫይረሱን ለመከላከል፣ ሕፃናት እና አዛውንቶችም ለዚህ ቫይረስ እንዳይጋለጡ ለማድረግ ክትባቱ ይሰጣል።

## ምን ማድረግ አለብኝ?

ከዚህ ቀደም ልጃችሁ ክትባት ወደ ተከተበበት ቲፓት ሐላቭ መሄድ ያስፈላጋችኋል። ከዚህ በፊት ከልጃችሁ ጋር ቲፓት ሐላቭ ሄዳችሁ የማታውቁ ከሆነ በመኖሪያ ስፍራዎት አቅራቢያ ወደ አለው ቲፓት ሐላቭ መሄድ ተገቢ ነው።

በዕብራይስጥ፣ በእንግሊዘኛ፣ በዐረብኛ ቋንቋ በጽሑፍ ለቀረበ ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በጤና ሚኒስተር የኢንተርኔት ድረ ገጽ መመልከት እና መኅብኘት ይችላሉ።

**በዕብራይስጥ፣ በእንግሊዘኛ፣ በዐረብኛ እና በአማርኛ ቋንቋ የስልክ ተጨማሪ አገልግሎት ከፈለጉ "ኮል ሃብሪኡት" (የጤና ድምጽ) ወደ ተሰኘው የጤና ሚኒስተር የስልክ ጣቢያ በስልክ ቁጥር *5400 በመደወል መረጃ መቀበል ይቻላል።**